# መልክአ ጉባኤ ላይ የተጠየቁ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው



አዘጋጅ፡- በትረ ማርያም አበባው ካሣ

(የመጻሕፍተ ሊቃውንት፣ የመጻሕፍተ ብሉያትና የመጻሕፍተ መነኰሳት ትርጓሜ መምህር)

ነሐሴ ፳፪፣ ፳፻፲፫

## መልክአ ጉባኤ ላይ የተጠየቁ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

**፩. መልክአ ሰንበት ላይ "ሰአሊ ለነ ሰንበተ ክርስቲያን ቅድስት ለውሉደ ሰብእ መድኃኒት ለዓለመ ዓለም ሰፋኒት" ይላል። ሰንበት እንዴት ሆና ነው ልትለምንልን የምትችለው?**

መልስ፦ ይህንን የመሰለ አነጋገር በመጽሐፍ ቅዱስም ተገልጿል። "ቀን ለቀን ነገርን ታወጣለች። ሌሊትም ለሌሊት ዕውቀትን ትናገራለች" ይላል (መዝ.18፥2)። በዚህ እንደምናስተውለው ዕለት ተናጋሪና ሰሚ ሆና ቀርባለች። ዕለት ግን ብቻውን ህልውና ያለው ነገር ስላልሆነ [ጥገኛ ሀላዊ በመሆኑ] መናገርም መስማትም አይችልም። በዚህ መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ አጻጻፍ ስልት መሠረት ሰንበትን ለምኝልን ብሏል። ፍሬ ሐሳቡ ግን ጌታ ሆይ በሰንበተ ክርስቲያን ያደረግኸውን የማዳን ሥራ አስበህ ይቅር በለን ማለት ነው።

**፪. ለአንድ ቅዱስ ማነው መልክኡን መድረስ የሚችለው?**

መልስ፦ መልክእን የሚደርሱት ሰዎች የሚደርሱለትን የቅዱሱን ገድል ወይም ድርሳን በጥልቀት የሚያውቁ፣ በተጨማሪም መልካም ሥነ ምግባር ያላቸው ሰዎች ናቸው። ይህም ሆኖ ሕብረታዊት በሆነችው ቤተክርስቲያን ይዘቱ ተገምግሞ ይፈቀዳል።

**፫. ማሕሌተ ጽጌ ላይ ዘሰ ይብል አፈቅረኪ ላይ "ኢክርስቱን ውእቱ አይሁዳዊ ወሠርፀ እስጢፋ ሐሳዊ" ይላል። የትኛው እስጢፋ ነው?**

መልስ፦ ይህ እስጢፋ በአፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመን አካባቢ ተነሥቶ የነበረ ሰው ነው። ለቅዱሳን የጸጋ ስግደት አይገባም ይል የነበረ ሰው እንደነበረ ይነገራል። ሐሳዊ የተባለም ለዚህ ነው። [እስጢፋ ደግ ሰው ነበረ የሚሉም አሉ። የሆነ ሆኖ ሁሉን በሚያውቅ በፈጣሪ እጅ ስላለ አያከራክረንም]።

**፬. መልክአ ማርያም ላይ "አፍቅርኒ እንበለ ንትጋ ለብእሴ ደም ወሥጋ ዘየዐቢ እምዝ ኢየኀሥሥ ጸጋ" ይላል። እውነት ከዚህ የሚበልጥ ጸጋ የለም?**

መልስ፦ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ሁለት ዓይነት ሁሉ አለ። አንደኛው ፍጹም ሁሉ ነው። ፍጹም ሁሉ ለእግዚአብሔር ይነገራል (ዮሐ.16፥30)። ሁለተኛው አንጻራዊ ሁሉ ነው (1ኛ ሳሙ.18፥28)። ለቅዱሳን ይነገራል። ብዙውን ለመግለጽ የምንጠቀምበት ቃል ነው። ከፈጣሪ በታች ከፍጡራን በላይ ድንግል ማርያም ናት። ቅዱስ ጳውሎስ የቆሮንቶስን ሰዎች እንደወደዳቸው ሁሉ እርሷም እኛን መውደዷ ለእኛ ታላቅ ጸጋ ነው (2ኛ ቆሮ.12፥15)። ከእርሷ የበለጠ እግዚአብሔር ስላለ በእግዚአብሔር መወደድ ደግሞ የበለጠ ጸጋ ነው። ከላይ የተገለጸው ከፍጡራን አንጻር ነው እንጂ ከፈጣሪ አንጻር አይደለም።

፫. መልክአ ሥላሴ ለአእጋሪክሙ ላይ ሥሉስ ቅዱስ አማልክተ አዳም ወሔዋ ይላል፡፡ ሥላሴ አማልክት ይባላሉን?

መልስ፦ አዎ ይባላሉ፡፡ እግዚአብሔር በአካል ሦስት ነው፡፡ እያንዳንዱ አካል በአንድነት ስሙ መጠራት ይችላል፡፡ ለምሳሌ አምላክነት የአንድነት ግብራቸው ነው፡፡ ስለዚህ አብ አምላክ፣ ወልድ አምላክ፣ መንፈስ ቅዱስ አምላክ ይባላል፡፡ ይህ ሦስቱም በአንዱ ግብረ ባሕርያቸው አምላክ መባላቸውን ለመግለጽ አማልክት ይባላሉ፡፡ ይህንን የመሰለ "አጋዕዝተ ዓለም/ የዓለም ገዢዎች" ሲባሉም ይገኛል፡፡ አማልክት ስንል በየራሳቸው የሚኖሩና የማይገነዛዘቡ እንዳይመስለን ደግሞ አሐዱ አምላክ ይባላል፡፡

፬. መልክአ ሥዕል ላይ "ለመጸብሓዊ ማቴዎስ ማርያም እንተ ረሰይኪዮ ወንጌላዌ ማርያም ሆይ ቀራጩ ማቴዎስን ወንጌላዊ ያደረግሽው አንቺ ነሽ" ይላል፡፡ ድንግል ማርያም ናት ማቴዎስን ሐዋርያ ያደረገችው? ክርስቶስ አይደለምን? አንቲ ውእቱ ረዳኢተ ያዕቆብ በቤተ ላባ ያዕቆብ በላባ ቤት ሲኖር ሳለ የረዳሽው አንቺ ነሽ ይላል፡፡ ያን ጊዜ አልነበረች እንዴት?

መልስ፦ የክርስቶስ ሥጋ ከድንግል ማርያም የተነሣ ሥጋ ስለሆነ ማቴዎስን ክርስቶስ መረጠው ለማለት ማርያም መረጠችው ብሏል፡፡ ይህንን የመሰለ አገላለጽ ከመጽሐፍ ቅዱስም ይገኛል፡፡ ለምሳሌ ሙሴ የያዕቆብ ልጅ ይሁዳ ከሞተ ከብዙ ዘመን በኋላ "አቤቱ የይሁዳን ድምፅ ስማ ወደ ወገኖቹም አግባው እጆቹ ይጠንክሩለት በጠላቶቹ ላይ ረዳት ትሆነዋለህ" ብሏል (ዘዳ.33፥7)፡፡ የይሁዳን ልጆች በይሁዳ ገልጿቸዋል ማለት ነው፡፡ ከዚህም ማርያም ሆይ ቀራጩ ማቴዎስን መረጥሽው ማለቱ በእርሷ ከእርሷ የተወለደውን ጌታ ክርስቶስን ያመለክታል፡፡ ያዕቆብን በላባ ቤት የረዳሽው አንቺ ነሽ ማለቱም የልጇን ለእርሷ አድሎ በመስጠት ነው፡፡ ያዕቆብን በላባ ቤት የረዳው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ይህም በቃልነቱ ይነገራል፡፡

፭. መልክአ ተክለ ሃይማኖት ላይ "ሰላም ለዝክረ ስምከ ዘጥንተ ፊደሉ መስቀል፡፡ ስም ክቡር ወስም ልዑል ሲልና ተክለ ሃይማኖት ማቴዎስ በዓለ ቀዳማይ ወንጌል ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ የፊደሉ መጀመሪያ መስቀል ለሆነ ስምህ መታሰቢያ ሰላምታ ይገባል ማለቱ "ተክለ ሃይማኖት" ሲል የመጀመሪያዋ ፊደል "ተ" መስቀልን ትመስላለች ማለት ነው፡፡ ተክለ ሃይማኖት ማቴዎስ በዓለ ቀዳማይ ወንጌል የሚለው ምሳሌ ነው፡፡ ተክለ ሃይማኖትን በማቴዎስ መስሎታል፡፡ ከወንጌላውያን ቀድሞ የተጻፈ ማቴዎስ በመሆኑ በዓለ ቀዳማይ ወንጌል ተብሏል፡፡

፮. የመልክአ ማርያም መግቢያ ማርያምሰ ኀርየት የሚለው ለማርያም ድንግል እንዴት ሆነ?

መልስ፦ ማርያምስ የማይቀሟትን መልካም ዕድልን መረጠች የሚለው ቃል የተነገረው ለማርያም እኅተ አልዓዛር ነው፡፡ በወቅቱ ከማርታ ሥጋዊ ዝግጅት ይልቅ ለመንፈሳዊ

ትምህርት ተግታ ስለተገኘች በጌታ የተመሰከረላት ነው (ሉቃ.10፥42)፡፡ ይህ ለእመቤታችን ሲነገር ደግሞ ከፍጥረታት ሁሉ አንጻር ይተረጎማል፡፡ ድንግል ማርያም በምግባሯ ከፍጥረት ሁሉ በልጣ በመገኘቷ መልካም ዕድልን መረጠች ተብሏል፡፡

፱. መልክአ ማርያም ላይ "ለዘኢያፈቅረኪ እግዝእትየ ማርያም ውኩፈ ኢይኩን ጸሎቱ" የሚለው ርግማን አይመስልም?

መልስ፦ አዎ ርግማን ነው፡፡ ተገቢ ርግማን አለ፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስም ይህንን የመሰለ ይገኛል፡፡ "የእግዚአብሔርን ሥራ በቸልታ የሚያደርግ ርጉም ይሁን" እንዲል (ኤር.48፥10)፡፡ በሐዲስ ኪዳንም ቅዱስ ጳውሎስ የሚገባ ርግማንን ተናግሯል፡፡ "አስቀድመን እንዳልን እንዲሁ አሁን ሁለተኛ እላለሁ ከተቀበላችሁት የተለየውን ማንም ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን" እንዲል (ገላ.1፥9)፡፡ የመልክአ ማርያም ደራሲም ከዚህ መሠረታዊ ሐሳብ በመነሣት አንቺን የማይወድ የተረገመ ይሁን ብሏል፡፡ ብርሃንን የወለደችልንን ድንግል ማርያምን አለመውደድ መረገም ነውና፡፡

፲. መልክአ ዮሐንስ መጥምቅ ለእራኀከ ላይ ዮሐንስ ጸሊ ኀበ ሊቅከ ኢያሱ ይላልና እንዴት ነው?

መልስ፦ ዮሐንስ ሆይ ወደ መምህርህ ኢያሱ ጸልይ ማለቱ ወደ ክርስቶስ ጸልይ ማለቱ ነው፡፡ ኢያሱ ማለት መድኀኒት ማለት ነው፡፡ ኢየሱስ ማለትም መድኀኒት ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ ከመልክአ ዮሐንስ መጥምቅ ኢያሱ ያለው ኢየሱስ ነው ማለት ነው፡፡

፲፩. መልክአ ኢየሱስ ላይ ጌታችንን ነቢይ ወሐዋርያ ይላልና ይህ እንዴት ይታያል?

መልስ፦ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ሰውነቱ ሐዋርያ ነቢይ ይባላል፡፡ ነቢያት በጸጋ የሚያውቁትን እርሱ በባሕርዩ ዐውቆ ወደፊት ስለሚሆነው ነገር በመናገሩ ነቢይ ይባላል (ማቴ.24፥5-51)፡፡ ሐዋርያ መባሉ በዚህች ዓለም በሥጋ እየተመላለሰ አስተምሯልና ነው፡፡ "ከሰማያዊው ጥሪ ተካፋዮች የሆናችሁ ቅዱሳን ወንድሞች ሆይ የሃይማኖታችንን ሐዋርያና ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስን ተመልከቱ" እንዲል (ዕብ.3፥1)፡፡

፲፪. መልክአ ኪዳነ ምሕረት ላይ እንበለ ምግባር ባሕቱ እመ ኢይጸድቅ አነ ቦኑ ለከንቱ ኪዳንኪ ኮነ ሲል እንዴት ነው?

መልስ፦ ያለ ምግባር የማልጸድቅ ከሆነ በውኑ ኪዳንሽ ለከንቱ ሆነን የሚል ጥያቄያዊ ሐተታ ነው፡፡ የዚህ መልክአ ደራሲ ስለትሕትና ምግባር ባይኖረኝም በቃል ኪዳንሽ ተስፋ አደርጋለሁ ለማለት የተናገረው ነው፡፡ ቃል ኪዳን ብቸኛ የመዳኛ መንገድ ተደርጎ ባይወሰድም እግዚአብሔር በቸርነቱ ሰውን ከሚያድንባቸው መንገዶች ግን አንዱ ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ የቃል ኪዳንን ጥቅም ለማጉላት የተናገረው ነው እንጂ ሥነ ምግባር

አያስፈልግም ለማለት አይደለም። በተቻለን አቅም ሥነ ምግባር ኖሮን በቃል ኪዳንም ተስፋ ማድረግ ይገባል ማለት ነው።

፲፫. ማኅሌተ ጽጌ ላይ ምስለ እለ ሐጸቡ አልባሲሆሙ የሚላቸው እነማን ናቸው? በደመ በግዑ የሚለውስ?

መልስ፦ ልብሳቸውን በበጉ ደም ያጠቡ የሚባሉ ምእመናን ናቸው (ራእ.22፥14)። በግ የተባለ ክርስቶስ ነው። ምእመናን ልብሳቸውን በበጉ ደም ያጠቡ መባላቸው ሥጋዉን ደሙን የተቀበሉ ለማለት ነው።

፲፬. መልክአ ሥላሴ ለአክናፊክሙ ላይ ትምይንተ ሉቃ ትሩፍ ይላልና ሉቃ ማን ነው? ለአእጋሪክሙ ላይ አርጤምስ እና ዜውስ ምንድን ናቸው?

መልስ፦ ሉቃ የሚባል ቅዱስ ነው። አርጤምስና ዜውስ በቀድሞ ዘመን ሰዎች ያመልኳቸው የነበሩ የጣዖት ስሞች ናቸው (የሐዋ. ሥራ 19፥28፤ ።

፲፭. መልክአ ጴጥሮስ ወጳውሎስ ለአእዛኒክሙ ላይ መሥዋዕተ አምልኮ ትኩኑ ይላልና እንዴት ነው?

መልስ፦ ከዚህ መሥዋዕተ አምልኮ ያለው ሰማዕትነትን ነው። ለእግዚአብሔር የሚቀርቡ ብዙ የመሥዋዕት አይነቶች አሉ። ለምሳሌ የምስጋና መሥዋዕት አለ። "ናብእ መሥዋዕተ ስብሐት በኵሉ ጊዜ ለእግዚአብሔር ፍሬ ከናፍሪነ" እንዲል (ዕብ.13፥15)። እንዲሁም ሰውነትን ስለእውነት ብለን እስከ ሞት አሳልፎ መስጠት የአምልኮ መሥዋዕት ይባላል (ሮሜ 12፥1፤ ራእ.12፥11)። ይህም ለእግዚአብሔር እስከ ሞት ድረስ ታምኖ ሰማዕት መሆን ማለት ነው እንጂ ሰውን መሥዋዕት አድርጎ ማቅረብ ይገባል ለማለት አይደለም።

፲፮. መልክአ ሥላሴ ላይ ሰላም እብል ለንዋየ ውስጥክሙ ምሕረትክሙ ትሩፋተ ገድል ይኩነኒ ሥላሴ አምጣነ ትሩፋት አንትሙ ሶበ ሖርኩሰ  ከመ እሳተፍ ገድሎሙ ጊዮርጊስ ኢወሀበኒ መጠነ ነጥበ ጠል እምደሙ ወተክለ ሃይማኖት ከልአኒ ስባረ እምዐጽሙ ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ የዚህ መልክእ ደራሲ እንደ ጊዮርጊስ ሰማዕት ለመሆን እንደፈለገ እና እንደ ተክለ ሃይማኖትም በጸሎት እግሩ እስኪሰበር መጸለይ እንደሚሻ ያሳውቃል። ገድለ ጊዮርጊስን ስናነብ እንደምናገኘው ጊዮርጊስ ብዙ ጊዜ ሰማዕት እየሆነ ደሙ እንደፈሰሰ ይነግረናል። ገድለ ተክለ ሃይማኖትን ስናነብ ደግሞ ተክለ ሃይማኖት ከጸሎቱ ጽናት የተነሣ አንድ እግሩ እስከመቆረጥ እንደደረሰ ይነግረናል። የዚህ መልክእ ደራሲ ጊዮርጊስ ከደሙ የዝናም ጠብታ ያህል አልሰጠኝም ማለቱ እንደ ጊዮርጊስ ስለእውነት ጥቂት ደም አልፈሰሰኝም ማለቱ ነው። ተክለ ሃይማኖት ከአጥንቱ ስባሪ አልሰጠኝም ማለቱም ትሩፋቴ አጥንቴ እስኪሰበር አይደለም ማለቱ ነው። ስለሆነም ትሩፋቴ እንደነዚህ ታላላቅ

ቅዱሳን ስላልሆነ እኔን በሥራዬ በትሩፋቴ ሳይሆን በቸርነታችሁ ይቅር በሉኝ ማለቱ ነው።

፲፯. መልክአ ኢየሱስ ለኵርናዕከ ላይ ሱባኤ ሰንበታት ስሳ የሚለው እንዴት ነው?

መልስ፦ ዳንኤል ስሳ ሱባኤን እንደገባ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፏል። "ሰብዓተ ሰንበታተ ስሳ ወክልኤተ ሰንበታተ" ይላል (ዳን.9፥25)። አንድ ሱባኤ በዳንኤል ሰባት ዓመት ነው። ስሳ ማለቱ የተረፈ ትቶ በመቁጠር ነው እንጂ ሙሉ ቁጥሩ 69 ነው። 69×7=483 ዓመት ይሆናል። ከዔዋዌ በኋላ ኢየሩሳሌም መታነጽ ከጀመረችበት ጀምሮ እስከ ክርስቶስ ስቅለት ድረስ 483 ዓመት ነው። በክርስቶስ ስቅለት መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ ሙሉ በሙሉ ተወግዷልና ቀጥሎ በምጽአትከ ተነትመ አበሳ [ሰው በመሆንህ መርገም ተወገደ] ብሏል።

፲፰. ማሕሌተ ጽጌ ላይ ለዘኢይሰቲ ወይነ ምንትኑ ሕይወቱ። ሲራክ ይቤ እስመ ትፍሥሕተ ልብ ውእቱ የሚለው ቢብራራልኝ።

መልስ፦ ከዚህ ወይን የተባለው የክርስቶስ ደም ነው። ወይን ለማይጠጣ ሰው ሕይወቱ ምንድን ነው? ብሎ በጥያቄያዊ መልኩ ገልጾታል። ሕይወቱ ምንም ነው ማለት ነው። አንድ ሰው የክርስቶስን ደም ካልጠጣ የዘለዓለም ሕይወት የለውም ማለት ነው።

፲፱. መልክአ ቁርቆስ መጨረሻው አካባቢ በሰላመ መንፈስ ቅዱስ የሚለው ላይ "ኢየሉጣ ገነት ዘመዓዛኪ ጥዑም። ይትከዐው ውስተ አፉየ ሐሊበ አጥባትኪ ዮም" ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ከዚህ ወተት ያለው በትርጓሜ ቋንቋ ግሥ ነው። በቅኔ ቋንቋ ሰም ነው። በወተት የተመሰለው የእግዚአብሔር ቃል ነው። የጡትሽ ወተት [ሐሊበ አጥባትኪ] ያለው የእግዚአብሔርን ቃል የመጠበቋ ትሩፋት ነው። ስለዚህ ትሩፋትሽ በእኔም ይደር ለማለት በአፌ ይፍሰስ ብሏል። ይህንን የመሰለ በመጽሐፍ ቅዱስም ተገልጿል። "ጌታ ቸር መሆኑን ቀምሳችሁ እንደ ሆነ ለመዳን በእርሱ እንድታድጉ አሁን እንደ ተወለዱ ሕፃናት ተንኰል የሌለበትን የቃልን ወተት ተመኙ" እንዲል (1ኛ ጴጥ.2፥2)።

፳. መልክአ ሥላሴ ለጕርዔክሙ ላይ ሚካኤልኑ ለአውፅኦ ሥጋየ ጌሠ ወእመ አኮ ገብርኤል ወሀበኒ ነፍሰ ሲል እንዴት ነው?

መልስ፦ ይህም በጥያቄ መልክ የቀረበ አፍራሽ ንግግር ነው። ከላይ ጀምሮ ስንመለከተው ሥላሴ ሆይ በችግር እንድኖር ቸል አትበሉኝ አትተተውኝ [ኢትትኀየዩኒ ኢትኅድጉኒ] ብሎ ደራሲው ይናገራል። ይህም የሰው ልጅ ፈጣሪ እናንተ ሥላሴ ስለሆናችሁ እናንተ ርዱኝ ማለቱ ነው። የፈጠራችሁኝ እናንተ ናችሁ እንጂ ገብርኤልም ነፍስን አልሰጥኝም ሚካኤልም ሥጋዬ እንዲወለድ አላደረገም የሥጋዬም የነፍሴም ፈጣሪ እናንተ ሥላሴ ናችሁ ማለቱ ነው።

**፳፩. መልክአ ሥላሴ ለህላዌክሙ ላይ "...መለኮተ ለለአሐዱ ዘዚአክሙ ገጻተ" ሲል መለኮትን ወደ ዮሐንስ ተዓቃቢ ክሕደት አይወስድም ወይ?**

መልስ፦ አይወስድም:: አረዳዳችንን ማስተካከል ነው:: አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ መለኮት አላቸው:: በአንዱ መለኮት ደግሞ እያንዳንዳቸው ይጠሩበታል:: አብ መለኮት፣ ወልድ መለኮት፣ መንፈስ ቅዱስ መለኮት ይባላሉ:: የምንቀበለው የክርስቶስ ሥጋ ሥጋ መለኮት መባሉ በዚህ አግባብ ነውና:: መለኮተ ለለአሐዱ ማለቱ እያንዳንዱ አካላት ስለሚጠሩበት ነው:: ዘዚኣክሙ ገጻተ የሚለው ደግሞ እየራሳቸው መልክ ገጽ ያላቸው መሆናቸውን ያመለክታል:: ለዚያ ነው ቀጥሎ "እንበተ ትድምርት እሰሚ ወእሁብ ትድምርተ" ያለው:: እንበለ ትድምርት እሰሚ ለአካላት፣ ወእሁብ ትድምርተ ለመለኮት ነው:: ለመለኮት ትድምርት ሲነገር ተዋሕዶ ነው:: ሥላሴ በተዋሕዶ ወተዋሕዶ በሥላሴ ከሚለው የሃይማኖተ አበው ቃል ጋር ይገናኛል::

**፳፪. በቤተክርስቲያን የቅዱሳን መላእክት መልክአ እንዴት ነው የሚታየው? ማለቴ ለአዕይንቲከ ለልብከ ብሎ እንደ ሰው ሲደረስላቸው የሰውን የሚመስል መልክ አላቸው ማለት ነው?**

መልስ፦ የመላእክት መልካቸው ልዩ ልዩ ነው:: የመልክእ ደራሲዎች ለመላእክት በሰው አምሳል መልክእ የደረሱላቸው በሰው አምሳል ስለሚገለጹላቸው በተገለጹላቸው ነው:: ሩፋኤል ለጦብያ፣ ገብርኤል ለማርያም የተገለጹላቸው በሰው አምሳል ነውና:: እነርሱን አብነት በማድረግ ለሰው ባለው መልክ ምሳሌ እያደረጉ መልክእ ጽፈውላቸዋል::

**፳፫. መልክአ ዮሐንስ ለኵልያቲከ ላይ ዮሐንስ ካህን ኃጢአተ ዓለም ኀዳጊ፣ በአስተሐምሞ ያስተበፅዐከ ዮጊ፣ ሊቀ ሰማዕታት ኀያል እትኩ ጊዮርጊ የሚለው ምን ለማለት ነው?**

መልስ፦ ዮሐንስ ካህን ኃጢአተ ዓለም ኀዳጊ የሚለው ዮሐንስ ካህን መሆኑን ያመለክታል:: ካህናት ደግሞ በብሉይም በሐዲስም ኃጢአትን ያስተሠርዩ ዘንድ ከእግዚአብሔር ሥልጣን ተሰጥቷቸዋልና ነው:: የሰማዕታት አለቃ ጊዮርጊስ በትኃት ንዑድ ክቡር ይልሀል ማለቱ አንዱ ቅዱስ ከእርሱ በፊት የነበረውን ቅዱስ ስለሚያከብር ነው:: ጊዮርጊ ያለው ጊዮርጊስ ለማለት ነው:: ይህ ከፊለ ስም ይባላል::

**፳፬. መልክአ ኪዳነ ምሕረት ለፀአተ ነፍስኪ ላይ እመደንግፃን ሠለስቱ ይላል:: ሠለስቱ ያላቸው እነማን ናቸው?**

መልስ፦ ሦስቱ የሚያስደነግጡ የተባሉት በመጽሐፈ መነኰሳት ፊልክስዩስ ላይ እንደተገለጹት "ፀአተ ነፍስ እምሥጋ [የነፍስ ከሥጋ መለየት]፣ ከጌታ ፊት መቆም እና ከጌታ ፍርድን መቀበል" ናቸው (ተስእሎ 152):: የመልክአ ኪዳነ ምሕረት ደራሲም አንዱን አመ ይፈልጠኒ ሞት እምሥጋየ ዝንቱ ብሎ ጠቅሶታል::

**፳፭. መልክአ አረጋዊ ለሐቋከ ላይ አረጋዊ ትብለከ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት፡፡ ለከ ይደሉ እግዚኦ በጽዮት ስብሐት ሲል ምን ለማለት ነው?**

መልስ፦ ለከ ይደሉ እግዚኦ ስብሐት በጽዮን [አቤቱ ለአንተ በጽዮን ምስጋና ይገባል] የሚለው መነሻው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃሉ ለእግዚአብሔር የተነገረ ነው፡፡ ለእግዚአብሔር ሲነገር ይህ የባሕርይ ነው፡፡ ለአረጋዊ ሲነገር ደግሞ የጸጋ ነው፡፡ ቅዱሳን የጸጋ ምስጋናን ይመሰገናሉና፡፡ ራሱ ጌታም የአባቴ ቡሩካን ብሎ አመስግኗቸዋል (ማቴ.25፥34)፡፡ በዘመናቸው ሁሉ እርሱን በደስታ ሲያገለግሉ ኖረዋልና፡፡

**፳፮. መልክአ ሥላሴ ላይ ለዘበነጊድ ላይ ዐሠርቱ አህጉር ያላቸው ምን ምን ናቸው?**

መልስ፦ ዐሠርቱ አህጉር የሚላቸው ዐሥሩ የቅድስና መዓርጋት ናቸው [አረጋዊ መንፈሳዊ ድርሳን 24]፡፡ ደራሲው በቅድስና መዓርግ ያሸበረቀ ይሆን ዘንድ ሥላሴን መለመኑን ያመለክታል፡፡ ሹመኝ ማለቱ ዐሥሩን የቅድስና መዓርጋት በየደረጃው እንድፈጽማቸው እርዱኝ ማለቱ ነው፡፡

**፳፯. ሰላም ለአዕዛንኪ ላይ ለእግዚአብሔር እግዚእ ሶበ ለገብርኤል ተመሰሎ ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ እግዚአብሔር ወልድ ገብርኤልን ይመስላል ይባላል ተብሏልም (ዳን.3፥92)፡፡ ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም ገብርኤልን መስሎ በአካለ ገብርኤል አድሮ ደስ ይበልሽ እያለ የምሥራች ነግሯታልና ይህንን ለመግለጽ ሶበ ለገብርኤል ተመሰሎ ብሏል (1ኛ ቆሮ.11፥1)፡፡

**፳፰. ሰላም ለመከየድኪ ላይ "ማርያም ጽዮን ታቦተ ቃለ ጽድቅ መን*ፈ/ቀ ዕሥራ ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ መንፈ*ቀ ዕሥራ (የኻያ ግማሽ) ዐሥር ነው፡፡ ስለዚህ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ዐሥሩ ትእዛዛት የተጻፉብሽ ታቦት ነሽ ይላታል ማለት ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ታቦት የድንግል ማርያም፣ ቃሉ የተጻፈበት ጽሌ የክርስቶስ ምሳሌ ነው፡፡

**፳፱. ማርያም ሆይ መልአክን ሕፃንን ከመቅሰፍ ርኅራኄሽ አስትቶታል ይላል፡፡ እንዴት ብሎ ነው ከማርያም ርኅራኄ የተያያዘው? መላእክትስ ከዲያብሎስ በኋላ (ጽነት) ወጪ ወራጅ ሐሳብ አላቸው?**

መልስ፦ መላእክት ከሳጥናኤል ጋር የነበረውን ጦርነት ካሸነፉ በኋላና በምሥራቅ የታያቸው ብርሃን ዕውቀት ከሆናቸው በኋላ ወጭ ወራጅ ኅሊና የላቸውም፡፡ ወዝንቱ ብርሃን ኮኖሙ ጥበበ ወአእምሮ እንዲል፡፡ ሕፃናትን ሊቀስፉ ሲላኩም መልአኩ ለእግዚአብሔር አልታዘዝም ብሎ ባለመታዘዝ አይደለም ያልቀሰፈው፡፡ የሳሙኤል ዘደብረ

ቀልሞን ክብሩ ይገለጽ ዘንድ፣ የመላእክትም ርኅራኄ ይገለጽ ዘንድ የተደረገ ነው እንጂ። መላእክት ርኅሩኅ ለመሆናቸውም በወንጌል በምሳሌ ተገልጿል። "ለአንድ ሰው በወይኑ አትክልት የተተከለች በለስ ነበረችው ፍሬም ሊፈልግባት መጥቶ ምንም አላገኘም። የወይን አትክልት ሠራተኛውንም እነሆ ከዚህች በለስ ፍሬ ልፈልግ ሦስት ዓመት እየመጣሁ ምንም አላገኘሁም ቁረጣት ስለ ምን ደግሞ መሬቱን ታጎሳቁላለች? አለው። እርሱ ግን መልሶ ጌታ ሆይ ዙሪያዋን እስክኰተኩትላትና ፋንድያ እስካፈስላት ድረስ በዚች ዓመት ደግሞ ተዋት" እንዲል (ሉቃ.13፥6-8 ትርጓሜ)። አሁን በዚህ ምሳሌ ለወይኒቱ ከባለቤቱ ይልቅ ሠራተኛው አስቦ አይደለም። በእግዚአብሔርና በመላእክት ያለውን ምሳሌ እንድንረዳ ነው እንጂ። እግዚአብሔር በባሕርዩ ቸር ስለሆነ ራሱ መሐሪ ሆኖ ሳለ የመላእክትን ባለሟልነትም እኛ እንድንረዳ እነርሱ ሲለምኑት ይስተዋላልና። ያንን ሕፃንም ቅሰፈው ብሎ ቢልከው አለመቅሰፉ ጌታ ሆይ ይቅር በለው የሚል ተግባራዊ ልመና ነውና። የቀውስጦስ ርኅራኄ የእርሷም ርኅራኄ በመሆኑ ርኅራኄኪ ድንግል ብሏል።

፴. መልክአ ተክለ ሃይማኖት ለግንዘተ ሥጋከ ላይ አድኅነኒ እምጸብአ አርዌ ዘዐሥር ቀርኑ ይላል። ዐሥር የተባሉ እነማን ናቸው?

መልስ፦ ዐሥር ቀንድ ያለው አውሬ የተባለ ዲያብሎስ ነው (ራእ.12፥3)። ዐሥር ቀንድ የተባሉት ሐሳዊ መሢሕ በሚመጣ ጊዜ የሚሾማቸው ዐሥር ነገሥታት ናቸው።

፴፩. መልክአ ማርያም ለአጻብእኪ ላይ እምኍልቈ ሠላስ ወስብዕ እንዘ ኢየሐጸ የሚለውና ዘአእጋርኪ አጻብአ ላይ ሐሳበ ኍልቆን ዘኮነ ምስለ ስድስ ርብዓ የሚለው ላይ አምስት አምስት ተብሎ ከመገለጽ ይልቅ በዚህ ድምር መልክ መገለጹ የተለየ ትርጉም አለው?

መልስ፦ የመልክእ ድርሰት ቤት እየመታ የሚሄድ ነው። ዘአእጋርኪ አፃብዐ ላይ "ምስለ ስድስ ርብዐ" ያለው ቤቱ እንዲገጥምለት ነው። ፍሬ ነገሩ ተደምረው ዐሥር ለሚሆኑ የእጆችሽ ጣቶች ሰላም እላለሁ ማለቱ ነው። 3+7፣ 4+6 ሁለቱም ዐሥር ስለሆኑ ደራሲው ለድርሰት እንዲያመቼው በየድርሰቱ እንደሚመቸው አድርጎ ጽፏል። ሌላም ሰው ምስለ ስብዕ ሥልስ፣ ምስለ ርብዕ ስድስ፣ ምስለ ስምን ክልአ...እያለ ቢደርስ ምንም የሚያመጣው ለውጥ የለም።

፴፪. ስብሐተ ፍቁር ላይ እምቅድመ ሰማያት ወምድር ሀልዎትኪ። ፀሐይ ወወርኅ ኢቀደሙኪ መላእክተ ሰማይ ይትለአኩኪ ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ይህ የድንግል ማርያም ሀልውና በመታሰብ ነው እንጂ በአካል ቅድመ ዓለም ነበረች ማለት አይደለም። ፀሐይ ወወርኅ ኢቀደሙኪ ማለቱ ፍጥረት ሁሉ በመታሰብ አንድ ስለሆነና ስለማይበላለጥ ነው። መላእክተ ሰማይ ይትለአኩኪ የሚለው ጌታቸውን ወልዳላቸዋለችና የጸጋ ምስጋናን ያመሰግኗታል ማለት ነው።

፴፫. መልክአ ኢየሱስ ለከናፍሪከ ላይ ይትከአው ውስተ አፉየ ከመ አዜባዊ ውሒዝ ሲል አዜባዊ ውሒዝ ምንድን ነው?

መልስ፦ አዜብ ማለት ደቡብ ማለት ነው። የደቡብ ነፋስ ጽኑዕ ነፋስ እንደሆነ ጠቢቡ ሰሎሞንም በተግሣጹ ጽፏል። "ደቡባዊ ነፋስ ጽኑዕ ወበስሙሰ ዘየማን ይሰመይ። ከወደ ደቡብ የመጣ ነፋስ ጽኑ ነው። በስሙ ግን ቀኝ ይባላል" እንዲል (ተግ.3፥16)። ስለዚህ ነቅዐ ገቦከ ደምህ በአፌ በጽኑ ይፍሰስ ማለት ነው። ይህም ደምህን ለመጠጣት የተገባሁ አድርገኝ ማለት ነው።

፴፬. ተአምረኪ ነጸረት ሳቤላ ያለው ተአምሩ ምንድን ነው? ሳቤላስ ማን ናት?

መልስ፦ ተአምሩ አልተገለጸም። ሳቤላ ያላት ግን በቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ የተገለጸችዋ በንጉሥ ሰሎሞን ዘመነ መንግሥት የነበረች ነቢዩት ናት።

፴፭. ሰላም ለአእናፊከ መዐዛ አርያም እለ ተመልኡ ይላል። ለምን ተመልኣ አላለም?

መልስ፦ እጆች፣ እግሮች፣ ተራሮችና የመሳሰሉት ነገሮች በራሳቸው ፆታ ያላቸው ስላልሆኑ በሴት አንቀጽም በወንድ አንቀጽም ይነገራሉ። ስለዚህ ከዚህ በብዙ ወንድ አንቀጽ ተመልኡ ይላል። ደራሲው መልክኡ ቤት እንዲመታለት ያደረገው ነው። ተመልኣ ቢልም የምሥጢር ለውጥ አያመጣም።

፴፮. ሐዋርያ ልደት ገብርኤል ለበለዓም ኮከበ ሕልሙ ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ በልዓም ጠንቋይ ቢሆንም እግዚአብሔር ፊቱን ጸፍቶ አፉን ከፍቶ ትንቢት አናግሮታል። "ይሠርቅ ኮከብ እምያዕቆብ ወይትነሣእ እምእስራኤል" እንዲል (ዘኍ.24፥16)። ደራሲው ቅዱስ ገብርኤልን በለዓም በሕልሙ ባየው ኮከብ መስሎታል። ያ ኮከብ ብሩህ እንደሆነ መላእክትም ብሩሃነ አካል ወአእምሮ ናቸውና። ሐዋርያ ልደት የሚለው ትወልዲ ወልደ ብሎ ለመናገር የተላከ በመሆኑ ነው።

፴፯. ሰላም ለዝክረ ስምከ ዘፊደለ አሌፍ ጥንቱ ወዘፍጻሜሁ በዝንቱ ይላል። መጀመርያው እንዴት ብሎ ነው አሌፍ የሆነው? ዐቢየ እግዚእ ሲል ዐ ዓይኑ ናትና።

መልስ፦ አዎ ይህ የምሥጢር ባይሆንም የፊደል ስሕተት ግን አለበት። ምናልባት ደራሲው ድምፀ ፊደሉን [Phonetics] ብቻ መሠረት አድርጎ ተናግሮት ይሆናል እንጂ ቅርጸ ፊደሉን [Morphology] መሠረት ቢያደርግ ኖሮ "ዘፊደለ ዐዩን [ዔ] / ע / ጥንቱ" ቢል በቀና ነበር። ወዘፍጻሜሁ በዝንቱ የሚለው መልካም ነው። መጨረሻው "እ" አልፋው አ /א/ ነውና።

፴፰. ተፈሥሒ ማርያም ንዒ ማርያም ላይ ብፁዕ ብእሲ ድቀተ ፀሩ ዘይሬኢ ይላል። ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ይህ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ "ጻድቅ በቀልን ባየ ጊዜ ደስ ይለዋል" ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው (መዝ.57፥10)። አሁን ጻድቃንም፣ እግዚአብሔርም በቀለኞች ቂመኞች ሆነው አይደለም። ያጠፋ ሰው በትክክለኛ ፍርድ መከራ ይደርስበታልና ትክክለኛ ፍርዱን በቀል ብሎት ነው። ጻድቃንም ትክክለኛ ፍርድን አይተው ደስ ይላቸዋል ለማለት ነው።

፴፱. መልክአ ፍልሰታ ላይ ድንግል ማርያምን ወለተ ማቲ ይላታል። ማቲ ማን ነው? ከዚሁ ጋር አብሮ ወርቀ አፌር ሲልስ አፌር ምንድን ነው?

መልስ፦ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ማትያን የሚባል የአያቷ ወንድም ስላለ ነው። በወንድም መጠራት ደግሞ መጽሐፋዊ ልማድ ነው። ማትያን የአያቷ የቅስራ ወንድም ነው። ማትያን የሚለውን ነው በከፊል ስም ማቲ ያለው።

፵. ሰላም ለዝክረ ስምከ ስመ መሓላ ዘኢይሔሱ ዘአንበረ ቅድመ እግዚአብሔር በአትሮንሱ ሲል እንዴት ነው?

መልስ፦ እግዚአብሔር አስቀድሞ በዙፋኑ ያስቀመጠው የመሓላ ስም ለሆነው የስምህ መታሰቢያ ሰላም እላለሁ ማለት ነው። እግዚአብሔር አስቀድሞ በዙፋኑ ያስቀመጠው የሚለው በኢያሱና በባሕርዩ ይተረጎማል። በኢያሱ ሲተረጎም ምሳሌውን ኢያሱን አስቀድሞ በማንገሥ የኢየሱስን መድኀኒትነት የገለጸክ ማለት ነው። ለባሕርዩ ሲነገር አስቀድሞም በባሕርዩ መድኀኒት ለሆነ ስምህ ሰላም እላለሁ ማለት ነው።

፵፩. መልክአ ሥዕል ሰጊድ ወአምኃ ላይ ወይነ በርተሎሜዎስ አንቲ ማርያም ዘያስተፌሥሕ ጣዕመ ፍቅርኪ ይላል በርተሎሜዎስ ማን ነው?

መልስ፦ ሐዋርያው በርተሎሜዎስ ነው። በርተሎሜዎስ በሐዋርያነቱ ጊዜ በወይን አፀድ ላይ ወይንን የሚንከባከብ ሐዋርያ ነው። ከወይን አፀድ ወይን ይገኛል። ከድንግል ማርያምም ወይነ ሕይወት ክርስቶስ ተገኝቷልና የበርተሎሜዎስ ወይን ተብላ ትጠራለች (ስንክሳር መስከረም 1)።

፵፪. እመ ተሰቅለ ቁልቁሊተ ወተተክለ በርእሱ እንበለ ረድኤትኪ አልቦ ዘይክል አድኅኖተ ነፍሱ የሚለው የማሕሌተ ጽጌ ሐሳብ ምን ለማለት ነው? አንዳንዶች ይህን ሐሳብ "ያለ እመቤታችን አማላጅነት ዓለም አይድንም" ለሚለው ይጠቅሱታል። ዘርዘር አድርገው ቢመልሱልኝ።

መልስ፦ ማንኛውንም ዐረፍተ ነገር ስንመለከት ዐውዱን መመልከት አስፈላጊ ነው። ያለእመቤታችን አማላጅነት ዓለም አይድንም የሚለው ሐሳብ የቅዱሳንን አማላጅነት ማመን ዶግማ መሆኑን ይገልጽልናል። እርሷም የጌታ እናት ቅድስት በመሆኗ የእርሷን አማላጅነት ያላመነ አይድንም ማለት ነው። ይህ ከፍሎ አማኝነት ነውና። የሰው ልጅ ለመዳን በእግዚአብሔር ማመን ዋናውና መደበኛው ነው። ቀጥሎ እግዚአብሔር ያከበራቸውን ማክበር አለበትና ነው። ሰው በራሱ እስከ መተከልና እስከ መሰቀል ደርሶ

ምግባር ቢሠራም ሃይማኖት ከሌለው እንደማይድን ያሳውቃል። ሃይማኖት ያለ ምግባር፣ ምግባር ያለ ሃይማኖት አይጠቅምምና። የድንግል ማርያም ረድኤቷ የጸጋ ነው። በባሕርዩ የሚረዳን ግን ራሱ እግዚአብሔር ነው። ያለእርሷ በቀር የሚለው ግን ከፈጣሪ በተለየ ነው። እርሷን ከፈጣሪ አስበልጦ ያለእርሷ አይድንም የሚል እሳቤ ካለ ግን ፍጹም ስሕተት ይሆናል።

፴፫. ተሰፍዎ ባዕድ አልብየ ዘእንበሌኪ ምክሕየ በኢመንኖ በልኒ ገብርየ ገብርየ ዘተሣይጥኩከ በንዋይየ። ማርያም ሆይ ከአንቺ ውጭ ሌላ ተስፋ የማደርገው የለኝም። እኔን ባለመናቅ/ባለመተው በገንዘቤ የገዛውህ ባሪያዬ አገልጋዬ በይኝ ይላል። ማርያም በየትኛው ዋጋ ነው የገዛችን? በሄጥ ተሣየጠክሙ ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር በሥጋክሙ ከሚለው ጋር አይጋጭም ወይ? ያለ አንች ሌላ ተስፋ የለኝም ሲልስ ወይእዜኒ መኑ ተስፋየ አኮኑ እግዚአብሔር ከሚለው ጋር አይቃረንም?

መልስ፦ ከአንቺ ውጭ ሌላ ተስፋ የማደርገው የለኝም የሚለው ከፈጣሪ ቀጥሎ ነው። "በቀር" ወይም "እንበለ" ሦስት ዓይነት አለ። ይኸውም ፈጣሪ ለፈጣሪ፣ ፈጣሪ ለፍጡራን፣ ፍጡራን ለፍጡራን ነው። ፈጣሪ ለፈጣሪ ስንል ለምሳሌ ምጽአትን በተመለከተ ወልድ ከአብ በቀር የሚያውቃት የለም ብሏል (ማቴ.24፥36)። ይህ በቀር ከፍጡራን ሲለየው ነው እንጂ አብ አውቋት ወልድ የማያውቃት ሆኖ አይደለም። ወልድም ሐዋርያትን ያለእኔ (እንበሌየ) አልቦ ዘትክሉ ወኢምንትኒ [ምንም ማድረግ አትችሉም] ብሏቸዋል። ይህ እንበለ ከፍጡራን ለመለየት እንጂ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ለመለየት አይደለም። ሁለተኛው ፈጣሪን ከፍጡራን ለመለየት የምንጠቀመው እንበለ [በቀር] ነው። "እኔ እግዚአብሔር ነኝ ከእኔ ሌላም [እንበሌየ] የሚያድን የለም" እንዲል (ኢሳ.43፥11)። ይህ የእግዚአብሔር የባሕርይ መሆኑንና የፍጡራን ግን የጸጋ መሆኑን የሚገልጽ ነው። ሦስተኛው የፍጡራን ለፍጡራን ነው። ይህ አንጻራዊ ነው ለምሳሌ ፈርዖን ዮሴፍን "...አነ ለልየ ፈርዖን ዘእንበሌከ አልቦ ዘእገብር ወኢምንተኒ ውስተ ኵሉ ምድረ ግብጽ" ብሎታል (ዘፍ.41፥44)። ዮሴፍ በፈርዖን ዘንድ ባለሟል [የተወደደ] በመሆኑ ዘእንበሌከ [ያለ አንተ] ምንም አልሠራም ብሎታል። እንዲያ ይበል እንጂ ያለ እግዚአብሔር ግን ማንም ምንም መሥራት አይችልም። ዮሴፍን የጠራው ከፍጡራን አንጻር ነው። ከዚህም ደራሲው የድንግል ማርያምን ባለሟልነት ለመግለጽ ያለአንቺ ተስፋ የማደርገው የለኝም ብሏል። በባሕርዩ ተስፋ የሚያደርገው ግን እግዚአብሔር መሆኑ ግልጽ ነው። ስለዚህ ወይእዜኒ መኑ ተስፋየ አኮኑ እግዚአብሔር ሲል በባሕርዩ ተስፋ የምናደርገው እግዚአብሔር ስለሆነ ነው። ድንግል ማርያምን ተስፋችን ነሽ ስንላት ደግሞ በተሰጣት ጸጋ እንደምትረዳን ተስፋ ስለምናደርግ ነው። ድንግል ማርያምን በገንዘቤ የገዛውህ ባሪያዬ በይኝ ማለቱ ደራሲው በባሪያ ተመስሎ ያቀረበው ምሳሌ ነው። በገንዘብ የተገዛን ባሪያ ባሪያዬ ባሪያዬ እንደሚሉት ሁሉ ለአንቺም ባሪያሽ ልሁንና

ባሪያዬ ባሪያዬ በይኝ ማለቱ ነው። ይህ ጽንዐ ፍቅሩን ያመለክታል። እንጂ በደሙ የገዛን አምላክስ አዎ ክርስቶስ ብቻ ነው።

፵፬. መልክአ ገብርኤል ለዝክረ ስምከ ላይ ጌታና አገልጋይ ይመስላል እንጂ የማይተረጎም ምሥጢር ለሆነው ስምህ መታሰብያ ሰላምታ ይገባል ይላል ምን ማለት ነው? ተተርጉሞ ሳለ የማይተረጎም አለው?

መልስ፦ ስም ብዙ ዓይነት ነው። የባሕርይ ስምን የሚገልጽ ስም አይገኝም። ለምሳሌ የነፍስ ነፍስ መባሏ የባሕርይ ስም አይደለም። የመልአክም መልአክ መባሉ የባሕርይ ስም አይደለም። የነፍስና የመልአክ የባሕርይ ስም እንደማይታወቅ ዮሐንስ አፈወርቅ ገልጿል (ድርሳን 2)። የመልክአ ገብርኤል ደራሲም የገብርኤል የባሕርይ ስም እንደማይታወቅ ለመግለጽ የማይተረጎም ምስጢር ብሎታል። እንደገና አገልጋይና ጌታ ብሎ መተርጎሙ ባሕርይ ባይታወቅም በግብረ ባሕርይ ስሞች ስለሚገለጽ ነው።

፵፭. ማሕሌተ ጽጌ ላይ አልቦ ጸሎት ወአልቦ ትንባሌ እንበሌኪ ማርያም ዘየዐርግ ሉዐሌ ይላል እንዴት ነው የማተረጎሞው?

መልስ፦ በመጽሐፍ ልማድ ብዙውን ሁሉ፣ ጥቂቱን አልቦ ማለት የተለመደ ነው። በዚህ አግባብ ራሷ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም "ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይለኛል" ስላለች ብዙው ምእመን የእርሷን የጌታ እናትነትና አማላጅነት አምኖ ስለሚኖርና በዚህም ነፍሳዊ በቊዔትን ስለሚያገኝ ያለአንቺ ልመና የሚያርግ ጸሎት የለም ተብሏል። ይህም በአንቺ ምልጃ የማይጠቀም የለም ማለት ነው። እርሷ ትማልዳለች የእርሷን ምልጃ ሰምቶ የሚምር ግን ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

፵፮. አትሮንሰ ሰሎሞን አንተ ለሐና ባሕርያ ንግሥታት ስሳ ወዕቁባት ሰማንያ ወዳሳኪ እንዘ ይገንያ። የሰሎሞን ስልሳ ሚስቶችና ሰማንያ ውሽሞች ዕቁባቶች እየሰገዱ አመሰገኑሽ ሲል ናሁ እምይእዜሰ ያስተበፅዑኒ ኩሉ ትውልድ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ዕፅዕት ይሉኛል ከሚለው ጋር አይጋጭም?

መልስ፦ ሰሎሞን በመሓልዩ ስሳ ንግሥታትና ሰማንያ ዕቁባ በሚሰግዱላት ሴት መስሎ የተናገረላት የዋሂት የድንግል ማርያም ምሳሌ ናት። ስትመሰልም ስሳ ነገሥታት የተባሉ 12ቱ ሐዋርያት ናቸው። አንዱን አምስት አንዱን አምስት አድርጎ ቆጥሮ ስሳ ይሆናል። ሰማንያ ያላቸው 72ቱ አርድእት ናቸው። ይህም የተረፈ ሞልቶ ነው። ስለዚህ ሐዋርያት አርድእት ድንግል ማርያምን ያመሰግኗታል ማለት ነው። እነርሱ ያመሰግኗታል ማለት ሌላው ሰው አያመሰግናትም ማለት አይደለም። ሌላው ሰውም ስለሚያመሰግናት ደግሞ ትውልድ ሁሉ ያመሰግነኛል ብላለች። ይህ ሁሉ አንጻራዊ ሁሉ ነው። ብዙ ሰዎች ያመሰግኗታል ተብሎ ይተረጎማል። ስለዚህ ምንም የሚቃረን ነገር የለውም።